

# በኤፌሶን የተነሳ ሁከት

- ጳውሎስ በኤፌሶን አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለና እርሱም እግዚአብሔር እንደሆነ ሌሎች ጣኦታት ግን ፍፁም አማልክት እንዳልሆኑ አስተማረ። በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ የኤፌሶን ነዋሪዎች ዲያና ተብላ የምትጠራውን ጣኦት ያመልኩ ነበር። የግሪክ ስሟ ደግ አርጤሚስ ይባላል።

- የዲያናን ምስል እያበጀ የሚሸጥ አንድ ዲሚጥሪስ የሚባል የእጅ ባለሙያ ወይንም ቀጥቃጭ ነበር። ምናልባትም የዲያናን ምስል በመሸጥ ከፍተኛ ሀብት ሳያካብት ታዲያ ጳውሎስን ለዚህ ከፍተኛ ሀብት ለሚያገኝበት ስራው እንደ ጠላት አደርጎ አየው። ስለዚህ በጳውሎስ ላይ ሕዝቡን በአመፅ አነሳሳበት። ሕዝቡም፣ “የኤፌሶኗ ዲያና ታላቅ አምላክ ናት፣” እያሉ ይጮኹ ይህንንም ደጋግመው ካሉ በኋላ ሕዝቡ መጮኽ ጀመር። በሕዝቡ መካከል ከነበሩት አንዳንዶቹ በምን ምክንያት እንደሚጮኹ እንኳን አያውቁም ነበር። ይጮኹ የነበረው ሌሎች ሲጮኹ ስለነበር ነው።

- ጳውሎስ ለሕዝቡ ንግግር ማድረግ ፈልጎ ነበር። ሆኖም በአጠገቡ የነበሩት ወዳጆቹ ጉዳት ሊደርስበት ይችላል ብለው በመፍራታቸው እንዳይናገር ከለከሉት። ጩኸቱ ለሁለት ሰዓት ያህል ቀጠለ። ከዚያም ወደአመፅ ተለወጠ። ከዚያም የከተማይቱ ባለስልጣን የሆነ አንድ ሰው ሕዝቡን ፀጥ እንዲል አደረገ። ሕዝቡ እንዲህ መጮኽና መረበሽ እንደማይገባውና ዲሚጥሪስ ችግር ካለበት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይለት እንደሚችል ገለጠላቸው።

- ባለስልጣኑ ሕዝቡን አሰናበተ። ጳውሎስም ምንም ጉዳት አልደረሰበትም።

*በኤፌሶን ስለተነሳው ሁከትና አመፅ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 19፡ 23- 41 ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ይቻላል።*

http://gardenofpraise.com